Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL



**ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ደወል ለተማሪዎች ሞባይል ስልክ መጠቀም አይፈቀድም**

# *የቤተሰብ እና የተማሪዎች መመሪያ*

**ለመማር ቅድሚያ መስጠት። የእያንዳንዱ ተማሪ በየቀኑ**

## የግል ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ከአጠገባቸው ራቅ ብለው ይቀመጣሉ ትምሕርት በሚሰጥበት ቀን ቀኑን በሙሉ

### ለምን

ስልኮችና ሌሎች የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች በትምህርት ቀን ትልቅ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። **እነዚህን ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ማራቅ ተማሪዎች በመማር ላይ እንዲያተኩሩ፣ እርስ በእርስ እንዲገናኙ፣ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የትምህርት ቤት ድባብ እንዲኖር ያግዛል።**

ሜሪላንድ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ከትምሕርት አመት 2027–2028 ጀምሮ የተማሪዎችን የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አጠቃቀም እንዲገድቡ የሚደነግግJoanne C. Benson Maryland Phone-Free School Act የተሰኘ ከስልክ-ነጻ የትምህርት ቤት ህግ አውጥቷል ስለዚህ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ እና ቤተሰቦች ለማስተካከል ጊዜ እንዲኖራቸው MCPS በዚህ አመት ሽግግር ማድረግ ይጀምራል።

### ተማሪዎች ማወቅ የሚያስፈልጋቸው ነገር

**ተማሪዎች ስልክ ወይም የግል ሞባይል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዘው መምጣት ይችላሉ — ነገር ግን ለጠቅላላው የትምህርት ቀን መጠቀም ስለማይፈቀድላቸው ራቅ ብሎ መቀመጥ አለበት።**

**ይህ ማለት የኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎቹ በሚከተሉት ጊዜያት ውስጥ ከተማሪዎች ርቀው ይቀመጣሉ ማለት ነው፡-**

**ክፍል ውስጥ • ኮሪደሮች • ወደ መማሪያ ክፍል መተላለፊያ ጊዜ • በምሳ ሠዓት • በእረፍት ጊዜ • መጸዳጃ ቤቶች በሚጠቀሙበት ጊዜ**

**ማድረግ ያለብዎት**

**✓ የትምህርት ቀን ከመጀመሩ በፊት ስልክና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎን አርቀው ያስቀምጡ።**
**✓ ከትምህርት ቤት የስንብት ደወል እስከሚደወል ድረስ አርቀው ያስቀምጡት።**
**✓ ሰራተኞች የሚሰጡትን መመሪያ ይከተሉ።**
**✓ አስተማሪ ሲነግር ከትምህርት ቤት የሚሰጠውን ቴክኖሎጂ ይጠቀሙ።**

### ማድረግ የሌለብዎት

**✗ ቴክስት፣ መደወል ወይም ማህበራዊ ሚድያ መጠቀም የለብዎትም**
**✗ ፎተግራፍ ማንሳት፣ ቪዲዮ መቅረጽ፣ ወይም ድምጽ መቅዳት አይፈቀድም።**
**✗ ከግል መሳሪያ ጋር የተገናኙ AirPods፣ ወይም የጆሮ ማዳመጫዎችን መጠቀም አይፈቀድም።**
**✗ በትምህርት ቀን ስማርት ሰዓት ወይም ሌላ የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጠቀም አይፈቀድም።**
**ከትምህርት ቤት በፊት? ✓ ከትምህርት ቤት በኋላ? ✓ በትምሕርት ቀን? አርቀው አስቀምጡት**

### ...ከሆነስ ምን ይሆናል?

- ያልተፈቀደ አጠቃቀም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የተማሪዎች ስነምግባር ደንብ ጋር የተገናዘበ የዲሲፕሊን እርምጃ ያስከትላል፣ እና **የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያው እስከ ትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ ተወስዶ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲቀመጥ ይደረጋል።**
- ተደጋጋሚ ጥሰቶች ተጨማሪ መዘዞችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፣ ይኼውም**የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት እስከማይፍቀድድረስ ውሳኔ ሊያሰጥ ይችላል ።**

**አስፈላጊ ልዩ ሁኔታዎች፡-** አንዳንድ ተማሪዎች ለ፡- IEP፣ 504 ፕላን፣ ከህክምና ጋር በተያያዘ ምክንያት ወይም ለሌላ የተፈቀደላቸው መገልገያ፣ ለድንገተኛ ወይም ለእንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ለቋንቋ ትርጉም ወይም ለሌላ ለተፈቀደ የትምህርት ዓላማ በተለይ ሲፈቀድላቸው የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጠቀም ይችላሉ።

በትምህርት ቤት ለጠፉ፣ ለተሰረቁ፣ ወይም ለተበላሹ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች MCPS ተጠያቂ አይሆንም።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች 2026